ብሔራዊ የምርጫ ዘመቻ የአካል ህዝባዊ መድረኮች

አስተባባሪ ኮሚቴ የሥራ መዝርዝር (ረቂቅ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ /ኢዜማ/ በ 2013 ዓ.ም በሚደረገው ሀገራዊ ምርጫ ጋር በተገናኘ ለምርጫው ዘመቻ አመቺነት ሲባል ካቋቋማቸው 13 ኮሚቴዎች መካከል አንዱ ህዝባዊ መድረኮችን የማስተባበር ሃላፊነት ያለበት ኮሚቴ ይገኝበታል። የኮሚቴው ስም፣ ዋና ተግባር፣ ዝርዝር ተግባራት እና የኮሚቴ-ተኮር ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. **የኮሚቴው ስም** - ብሔራዊ የምርጫ ዘመቻ የአካል ህዝባዊ መድረኮች አስተባባሪ ቡድን ይባላል።
2. **የኮሚቴው አቢይ ተግባር** - ኮሚቴው በአዲስ አበባ፣ ድሬድዋ፣ በክልል ከተሞች እና በዞን ከተሞች የሚደረጉ ህዝብ በአካል ተገኝቶ የሚታደምባቸው ስብሰባዎችን ማቀድ እና ማስፈጸም ላይ በዋናነት የሚሰራ ኮሚቴ ነው።
3. **የኮሚቴው ዝርዝር ተግባራት**
    1. ህዝባዊ ስብሰባዎች የሚደረጉበትን ቦታ እና ቀን መወሰን፣
    2. ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የሚገኙ መሪዎችን መመደብ፣
    3. በህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የሚቀርቡ አቅርቦቶች ይዘትን መፈተሽና ይሁንታ መስጠት፣
    4. ለህዝባዊ ስብሰባዎች የሚሆኑ አዳራሾች፣ የድምጽ ስርዓት ማሳለጫ ቁሳቁስ እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች ዝግጁ ማድረግ ወይንም መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
    5. ከስራው ጋር የተገናኙ ወጪዎችን በፓርቲው የፋይናንስ ስርዓት መሰረት በመያዝ ሪፖርት ማድረግ፣

4. **የኮሚቴ አባላትን የተመለከተ**
    1. ቡድኑ ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴዎች ይኖሩታል፣
    2. ኮሚቴው በሁለት ሣምንት አንድ ጊዜ ይገናኛል፣
    3. የኮሚቴው ጸሃፊ የኮሚቴውን ቃለ-ጉባዔ በመያዝ ለኮሚቴው አባላት በኢ-ሜል ይልካል፣
    4. ሠብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የኮሚቴው ጸሃፊ ለእለቱ ስብሰባ ሌላ ጸሃፊ በመሰየም የኮሚቴውን ስብሰባ ይመራል፣
    5. የኮሚቴው ሰብሳቢ ስለ ኮሚቴው ወቅታዊ መረጃዎችን ለኮሚቴው በስብሰባ መግቢያ ላይ በማቅረብ አጀንዳ ተኮር ወደ ሆኑ ስብሰባዎች ይገባል፣
    6. በውሳኔዎች ላይ ስምምነት በማይኖርበት ጊዜ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፣
    7. የኮሚቴው አባላት በስብሰባ ላይ እንዲታይ የሚፈልጉትን አጀንዳ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ከስብሰባው መጀመር ሁለት ሰዓት በፊት ማቅረብ ይችላሉ፣

Draft 1

8. በኮሚቴው የተሰጠውን ሃላፊነት በሚገባ እየተወጣ ያለ የኮሚቴ አባል በሚኖርበት ጊዜ ጉዳዩ በአጀንዳ ተይዞ ኮሚቴው ውሳኔ ካሳለፈ በኋላ የኮሚቴው ሠብሳቢ በሌላ አባል እንዲተካ ያደርጋል፣
9. የኮሚቴው ሥራ ጥር 13፣2013 ዓ.ም. ተጀምሮ ሰኔ 12፣ 2013 ዓ.ም. ይጠናቀቃል፣
10. የኮሚቴው የሥራ ዘመን ሪፖርት ላይ የኮሚቴው ማጠናቀቅ ወቅት ላይ በሚኖሩ አባላት በሙሉ የሚፈረምበት ይሆናል።

5. የኮሚቴው አባላት፣

የሚከተሉት ግለሰቦች የኮሚቴው አባላት ናቸው፣

1. ሐብታሙ ኪታባ ... ሠብሳቢ
2. አሉላ ተስፋዬ ... ጸሃፊ
3. መሳይ ታደሰ ... አባል
4. ሐይለገብርኤል አያሌው ... አባል
5. ናትናኤል መኮንን ... አባል
6. ስዩም መንገሻ ... አባል
7. ዋሲሁን ተስፋዬ ... አባል

Draft 1